# ቅንጅት መንፈሱ

የናንት መቀናጆ፣

አይታኘክ አንጆ፣

በአውቀት ያልተበጆ፣

በልምድ ያልደረጆ፣

ከአንቀልባው ሳይወርድ ስልጣን እንደባጆ፣

ይኸው በቡቃያው በጻዴው አረጆ::

የናንተው ቅንጅት፣ ድፍረት የተኩዋለ፣

ጥሞና የነሳው፣ መስከን ያልታደለ፤

እየተወሻሸ፣ እየተዛዘለ፣

ጥዋት ትግል ወጥቶ፣ ተሲያት ደከመ

"አለት መቀናጆው"፣ በ አፍላነቱ ላመ

ካስማው ተነቀለ፣ምሰሶው ዘመመ፤

"የትግል ጽናቱ" ፣ ጉልበቱ ለገመ

የትናንቱ ስተት፣ ዛሬም ተደገመ፣

በስልጣን ሽኩቻ፣ ጥምረቱ ታመመ::

ስልጣን በጅ፣ ስልጣን በጅ፣

ፍቅር እንዲደረጅ፣እፈረንጅ አገር ደጅ፣

ልክ እንዳገር ቤቱ፣ የምርጫ ቱማታ

ፓርላማ አንገባም፣ስልጣን ዛሬ መጥታ፣

መንበርዋን ካልጨበጥን፣ ጆንበር እንዴት ወጥታ

'እንኮዬ ድማሜ የልጆች ጨዋታ"

“ዶሮማታ፣ማታ፣”፣ ስልጣን ማታ፣ማታ

“የምን ስልጣን ማታ፣ይቺ ናት ጨዋታ!

ዛሬ እንጂ በጥዋቱ፣

ዲሞክራሲ ሂደቱ፣

ይደፋ ባናቱ፣

አረ የታባቱ!

ስልጣኑ እንዳሻነው፣ባንድ ጆምበር ይምጣ፣

ጆምበር ከጠለቀች፣ባፍንጫችን ይውጣ፣

ለምን ስልጣን ነገ፣ለዛሬ ነው ምጤ፣

ካልሆነ እዘፍናለሁ፣የፍየል ወጠጤ፣

መልኬ እንጂ ቅንጅት፣ግን ደርግ ነው ውስጤ”

ሆነና ነገሩ፣አካሄድ የነአጤ፣

ፓርላማውን ናቁት፣ባይሆናቸው ብጤ::

ዛሬም እንደገና፣ያቻምናዋ ብዋልታ፣

ሾረች ስደት መጥታ፣ አምራ ተቆናጅታ፣

“እንኮዬ ድማሜ፣የልጆች ጨዋታ፣”

“ዶሮ ማታ፣ማታ”፤ስልጣን ማታማታ፣

የምን ስልጣን ማታ፣በል ጆምር ቱማታ፣

ዘራፍ ተነካከስ፣ጆምበር ሳትመለስ፣

እርስ በርስ ተብዋቀስ፣

“ትግሉን እዳር አድርስ፣”

ተብዋቅሰህ ስትጨርስ፣

ደሞ ፊትክን መልስ፣

ወዲህ ወደ ሁዋይት ሀውስ፣

ወደ ነጩ ታቦት፣

ወደ አምልኮትህ ቤት፣

ተሰለፍ ለለቅሶ፣

ልትል ክላላይሶ፣

ደሞ ባንተ ብሶ፣

መንፈስ ማለት ደርሶ፣

ከሆነም ነው እርኩስ፣

የትም የት የማይደርስ፣

ያልረባ ለራሱ፣

ቅንጅት መንፈሱ::

አህዱ ሰላሙ

መስከረም16 2000 ዓ.ም.